# 5. የኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች

በመላው አገሪቱ በእያንዳንዱ የጤና አገልግሎት ክፍለህገር የመንደሩ ነዋሪዎችን የሚያገለግሉ የኩንላንድ የኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች፣ ይገኛሉ። በእያንዳንዱ የኮሚኒቲ ማእከል የሚሰጥ የአገልግሎት ዓይነት ይለያያል፡ ይህም ህዝቡ የሚያስፈልገው ነገር የተለያየ ስለሆነ ነው።

በአከባቢዎ የኮሚኒቲ የጤና መእከል ለማግኘት ወደ 13HEALTH ተሌፎን ቁጥር 13 43 25 84 ይደውሉ።

በኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች የሚቀርቡት አገልግሎች እና ስራዎች በኩንስላንድ የጤና አገልግሎት የገመገማሉ። ነገር ግን ቀጥሎ የተዘረዘሩት የጤና አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች በተለያዩ ቦታዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያሳዩ ናቸው፥

## የልጆች እና የወጣቶች የጤና አገልግሎቶች

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በተመለከተ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፡ ወደ የልጆች ጤና መስመር በ (07) 38622333 ወይም በ 1800 177 279 (ከብሪስባን ውጭ) ይደውሉ።

### የልጆች የጤና አገልግሎቶች እና ክሊኒኮች

- ከ0-12 ልጆች ላላቸው ወላጆች፡ ግምገማ፣ ትምህርት እና ድጋፍ ይሰጣል
- የጡት ምግብ መስጠት ድጋፍ
- የአዲስ ወላጆች ቡዱን እና የልጅ አስተዳደግ ፕሮግራሞች
- የክትባት ክሊኒኮች
- የአላይድ የጤና አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡ ኑሮሎጂስት፣ ሶሻል ዎርከር፣ ሳይኮሎጂስት)
- የመጀመርያ ትምህርት ማጣርያ
- አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤት በመሄድ መጠየቅ
- የልጆች ጤናማ የሆነ አስተዳደግና እድገት ይመረምራል እንዲሁም ያጣራል።

### በትምህርት ቤት የሚሰጥ የወጣቶች የጤና አገልግሎቶች

- ለወላጆች እና ከ13-18 ዕድሜ ላላቸው ወጣቶች፡ የስቴስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚሄዱ የጤና ቀጠሮ፣ ምርመራ፣ ድጋፍ፣ ስለ ጤንነት መረጃ፣ ወደ ሌላ መስተላለፍ እና ስለ ጤንነት ትምህርት መስጠት

### የልጅ እና የወጣቶች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች

- ከ0-18 እድሜ ያላቸው የአእምሮ ጤንነት መታወክ ችግር ላለባቸው ልጆች፡ ምክር፣ ግምገማ፣ ሕክምና እና እንክብካቤ

### የትምህርት ቤት የጥርስ እንክብካቤ አገልግሎቶች

- አራት እና ከዛ በላይ ዕድሜ ሆነው ነገር ግን 10 ላልሞሉ ልጆች የትምህርት ቤት የጥርስ እንክብካቤ ይሰጣል

## የአዋቂዎች የጤና አገልግሎቶች (18 እና ከዛ በላይ ዕድሜ ላላቸው)

ቀጥሎ ያሉትን አገልግሎቶች በተመለከተ የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፡ ወደ 13HEALTH በስልክ ቁጥር 13 43 25 84 ይደውሉ። አላይድ የጤና አገልግሎቶች በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት መረጃ ጽሑፍ 7 የአላይድ ጤና የሚለውን ይመላከቱ።

### ጠቅላላ የጤና ግምገማ፣ የክሊኒክ አገልግሎቶች እና ድጋፍ

- ነርሲን፣ ከሆስፒታል ከወጡ በኃላ የሚያገኙት እንክብካቤ እና የአላይድ የጤና አገልግሎቶች የሶሻል ዎርክ፣ ኦኩፔሽናል ቴራፒ፣ ፊዚዮ ቴራፒ እና ሳይኮሎጂን ያጠቃለለ

### ለሽማግሌዎች የሚሰጥ አገልሎች

- የግምገማ ቡዱን፣ የቤት እንክብካቤ፣ የቤትና የኮሚኒቲ እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ እና አንድ ሰው ከታከመ ወይም የቀዶ ጥገና ካደረገ በኃላ የመበረታታት እርዳታ መስጠት

### የኮሚኒቲ የማህበራዊ ኑሮ አገልግሎቶች

- የአላይድ የጤና አገልግሎት (ፊዚዮቴራፒ፣ ኦኩፔሽናል ቴራፒ፣ እና የንግግር ቴራፒ)

### የPalliative እንክብካቤ አገልግሎቶች

('የPalliative እንክብካቤ' ማለት በጠና ለታመሙ እና መሞታቸው የማይቀር ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ ማለት ነው።)

- በኮሚኒቲ የሚተዳደር የPalliative እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ መረጃዎች እና ትምህርቶች እና በሞት ጊዜ የሚደረግ እርዳታ።

### የአዋቂዎች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች

- ግምገማ፣ ሕክማን፣ እና የአእምሮ ችግር ላለባቸው አዋቂዎች እንክብካቤ መስጠት

### የአዋቂዎች የጥርስ እንክብካቤ አገልግሎቶች

- ለሚገባቸው አዋቂዎች ያለ ምንም ክፍያ የሚሰጥ የጥርስ ክሊኒክ (መረጃ ጽሑፍ 6 የጥርስ እንክብካቤ አገልግሎቶች የሚለውን ይመለከቱ)